## ኤችአየቪ ኖርዌ (HivNorge)

ኤችአቪ ኖርዌ ከኤችአቪ ጋር ለሚኖሩ እና ኑሮአቸውን ኤች አይ ቪ የሚነካ ግለሰቦችን በኖርዌ ውስጥ የሚገኝ ብቸኛ የሆነ የሕሙማን ድርጅት ነው ።እንደዚሁም በተጨማሪም በኤች አይ ቪ ተጠቂ ግለሰቦች ፣ እንዲሁም የፕራይፕ ተጠቃሚዎችን እና በኤች አይ ቪ የምመበከል እድላቸውን ከፍተኛ ለሆኑ ሰዎች ጨምሮም ላላቸው ማንኛውም ለፍላጎታቸውም ተቋርቋሪ የፖለቲካ ድርጅትም ነው ።

## ኤችአይ ቪ ምንድን ነው?

ኤች አይ ቪ በሽታን የሚከላከልን (immunforsvaret) የሰውነት ስርዓትን የሚያጠቃ ቫይረስ ነው ። ቫይረሱ ወደ ሰውነት ሲገባ የሰውነት የበሽታ መከላከያውን ቀስ በቀስ ያዳክማል ወይም ያጠቃል ይህንንም ጥቃት የሚቋቋም መድሃኒት ካልወሰዱ ሰውነትን ለበሽታ እና ለበሽታ መበከል ጥቃት ተጋላጭ ያደርጋል።

ኤድስ (AIDS)(የበሽታ መከላከያ የሰውነት ክፍል ድክመት ሲንድሮም / acquired immunodeficiencysyndrome) በኤች አይቪ የበሽታ መበከል ምክንያት በተዳከመ የሰውነት በሽታ የመከላከል አቅማቸው መድከም የተነሳ የሚከሰቱ ተመሳሳይ የሆኑ በርካታ በሽታዎችን የሚያጠቃልል የጋራ የመተጠሪያ ቃል ነው ። በኖርዌይ ውስጥ በጥቂቱ ስራ ላይ የዋለ የሕመም መጠሪያ ነው። ለኤች አይ ቪ መበከል ሕክምና ሲጀምሩ በሽታ የመከላከል የሰውነት ስርዓትዎ ይጨምራል እናም ከዚህ በኋላ የኤድስን የበሽታ ያለበት ግለሰብን መስፈርታት አያሟሉም ማለት ነው።

ከኤች አይ ቪ የሚያድን ወይም የሚፈውስ ህክምና የለም ። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የሚሰጠው ውጤታማ ህክምና ለከባድ በሽታ ችግሮች ተጋላጭነትን የሚቀንስ ከመሆኑም በላይ እንደዚሁም ሌሎችን የመበከል አደጋውንም ያስወግዳል ።

## የኢንፌክሽን መንገዶች እና እራስዎን እንዴት መጠበቅ ይችላሉ

በኤች አይ ቪ ጋር የሚሆሩ ግለሰቦች ወይም ሕሙማን እና እንደዚሁም ስኬታማ ህክምና ላይ የሚገኙ እና በደማቸው ውስጥ ተለኪያዊ የቫይረስ ቁጥር መጠን የሌላቸውን ግለሰቦች በኤች አይ ቪ ለሌሎች ማስተላለፍ አይችሉም ። ኤች አይ ቪ እንዲሁ በማኅበራዊ ግንኙነት ማለተም በመሳሳም ፣ በመተቃቀፍ ፣ አንድን ኩባያ በመጋራት ወዘተ ተላላፊ በሽታ አይደለም ።

ኤች አይ ቪ በዋነኝነት የሚተላለፈው ኤች አይ ቪ ካለበት እና ህክምና ላይ ከማይገኝ ሰው ጥንቃቄ የጎደለው ወሲባዊ ግኑኝነትን በመፈጸም ፣ ደም ከሌላ ሰው በማግኘት እና ከእናት ወደ ልጅዋ በእርግዝናዋ ፣ በመወለድ እና ጡት በምታጠባት ወቅቶች ሊተላለፍ ይችላል ።

ራስዎን ከኤች አይ ቪ ለመከላከል የሚያበቁ ብዙ ዘዴዎች አሉ

ስኬታማ ህክምና ፣ ኤች አይ ቪ ካለባቸው እና በተሳካ በቂ ህክምና ላይ ካሉ ሰዎች በኤች አይ ቪ የመበከል አደጋ የለውም ። ይህ ማለትም ግለሰቡ ህክምናውን ይከተላል ፣ መድሃኒቱን ይወስዳል እናም ስለሆነም የቫይረሱ ቁጥር እጅግ በጣም አነስተኛ በሆነ መንገዱ ሲጠበቅ ለማንም ማለትም ጥበቃ በሌለው ሁኔታ በፆታዊ ግንኙነትም ሆነ በእርግዝና ወይም በወሊድ ወቅቶች ሊተላለፍ የማችል ነው ።

## ስኬታማ ህክምና ለኤች አይ ቪ ሕክምና

የኤች አይ ቪ ሕሙማን በቂ በሆነና ስኬታማ ህክምና ላይ ካሉ ግለሰቦች ኤች አይ ቪን የመስተላለፍ አደጋ የለቸውም ። ይህ ማለትም ግለሰቡ ህክምናውን ይከተላል ፣አስፈላጊውን መድሃኒቱን ይወስዳል እናም ስለሆነም የቫይረሱ ቁጥር እህግ በጣም ጥቂት ስለሚሆን ጥንቃቄ ባልተጠበቀበትም ፆታዊ ግንኙነትም ሆነ በእርግዝና ወይም በወሊድ በሽታው ሊተላለፍ አይችልም ማለት ነው ።

ኮንዶም በኤች አይ ቪ እና በግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሚተላለፉ ሌሎች የአባለዘር በሽታዎች ከመበከል የሚከላከል ሲሆን በ**www.gratiskondomer.no** ከሚባለው ድሕረ ገጽ ያለ መንም ወጭ ኮንዶምን ማዘዝ ይቻላል ።

**ፕራይፕ** (**PrEP**) (ቅድመ-ተጋላጭነት መከላከያ ወይም preeksponeringsprofylakse) የኤች አይ ቪ መደሐኒት ሲሆን የኤች አ ቪ ተበካይ ላልሆኑ (hivnegative) ግለሰቦችን ከኤች አቪ በሽታ መበከል የሚጠበቅ እና የመንጠቀቂያ መድሐኒት ነው።

ፕራይፕን የሚባለውን መድሐኒት ለማግኘት ከመደበኛ ሐኪምዎት ወደ ኡላፍ ተመላላሽ ሆስቲፒታል (Olafiaklinikken) ወይም ወደ አካባቢዎ ለሚገኘው የለተላላፊ በሽታ መምርመሪያና ሕክምና በሚሰጥበት በአጥቢዎ ወደሚገኘው ሆስፒታል ሪፈራል ሊኖርዎት ብቻ ነው።

አንድ ግለሰብ ለከባድ በሽታ የመበከል የአደጋ ሁኔታ ከተጋለጠ ፣ ፒኢፒ (**PEP**)(ድህረ-ተጋላጭነት መከላከያ) ኤች አይ ቪ ቫይረስ ወደ ሕዋሳት እእንዳይገባ እና እንዳይባዛ የሚያግድ መድኃኒት ሊወስድ ይችላል ። **ፒኢፒን** (PEP)በተቻለ ፍጥነት ወዲያውኑ መውሰድ ሲያስፈልግ በተለይም ለኤች አይ ቪ ከተጋለጡ በሁላ እስከ 48 ሰዓታት ከማለፉ በፊት መወሰድ የግድ አስፈላጊ ነው ። ፒኢፒ መድህኒቱን ለ28 ቀናት መውሰድ ያስፈልጋል ። በኖርዌይ የሚገኙ ማንኛውም የአስቸኳይ ጊዜ ሕክምና አግልግሎት ሰጭ

ተቋማት (akuttmottak) እና እንደዚሁም በማንኛውም ታላላቅ ከተማ ውስጥ በሚገኝ የድንገተኛ ሕክምና ተቋማት (storbylegevakter) ፒኢፒን ወይም PEP የተላላፊ በሽታ ልዩ ባልሙያን ሀኪም ሳያማክሩን መድሐኒቱን መስጥት ይችላሉ።

## ለኤች አይ ቪ ምርመራ ማድረግ

በኤች አይ ቪ መበከልን ለማወቅ የሚቻልበት መንገድ የኤች.አይ.ቪ ምርመራ በማድረግ ብቻ ነው ፡፡ ይህ ምርመራ መደበኛ ሀኪም ተመላላሽ ክሊኒክ ፣ አንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ፣ ለወሲብ ጤና ጥንቃቄ እርዳታ የሚሰጥበት ተመላላሽ ሆስፒታል ማለትም እንደ አላፊያ ተመላላሽ ሆስፒታል (Olafiaklinikken) እና ወሲብ እና ማህበረሰብ (Sex og samfunn)(ከ25 ዓመት በታች ለሆኑ ብቻ ነው) ። ለኤች አይ ቪ ለመበከል ከፍተኛ ለሆነ አደጋ ተጋላጭነት ሁኔታ ሲያጋጥመው አንድ ግለሰብ የኤች አይ ቪ ምርመራን መውሰድ በነፃ ያለምንም ክፍያ ይሆናል ፡፡

ሁለት ዓይነት የምርመራ ዘዴዎች አሉ ፡፡ አንደኛው ተራ የደም ምርመራ ሲሆን መልስ ለማግኘት በግምት አንድ ሳምንት ይወስዳል። ብዙ ድርጅቶችም ፈጣን የምርመራ መልስ የሚገኝበት የምርመራ ዘዴ አገልግሎትን ይሰጣሉ በደዚህ አይነት ምርመራ የውጤቱ መልስ በደቂቃ ውስጥ ማግኘት ይችላሉ ፡፡ እነዚህም ለምሳሌ በጤና አገልግሎት ኮሚቴ (Helseutvalget)እና ደቂቃዊ ምርመራ (Minuttesten) ናቸው ፡፡

ለኤች አይ ቪ የተለከፉ ለአብዛኞቹ ግለሰቧች በበሽታው በተለከፉ ከ2-6 ሳምንታት በኋላ በምርመራው ላይ ሊታይ ይችላል ፡፡ ለጥቂት ግለሰቦች ግት ትንሽ ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ ይችላል ።ስለዚህም በበሽታው ለመለከፍ አደጋ ተጋልጠው ከነበረ ከ12 ሳምንታት በኋላ ምርመራውን ቢወስዱ የተሻል ሁኔታ ነው በማለት እናሳስባለን ።

### ምርመራው ውጤቱ አዎንታዊ ወይም ፖዘቲፍ ከሆነ

ለኤች አይ ቪ ምርመራው ውጤት አዎንታዊ ወይም ፖዘቲፍ ከሆን ወደ ተላላፊ በሽታ የጤና ተቋም ተልከው ይሕክምና እግልግሎት እንዲያገኙ እድል ይቀርብሎታል ፡፡ ከኖርዌይ ውስጥ ከኤች አይ ቪ በሽታ ጋር ለተያዙ ህክምናዎች በሙሉ በነፃ ይሰጣሉ ፡፡ ኤች አይ ቪ በአሁኑ ዘመን ሥር የሰደደ ዘላቂ የሆነ የህመም ሁኔታ ሲሆን እንደማንኛውም ሰው ግን ረጅም ዕድሜ ዘመን መኖር ይቻላል ፡፡ ሆኖም ግን ለዚህ ረጅም እድሜ ለመብቃት የኤችአይቪ ሕክምናውን ወዲያውኑ መጀመር እጅግ አስፈላጊ ነው ፡፡ ይህ ለራሱ ጥቅም ብቻ ሳይሆን በአንጻራዊ ሁኔታው ሲታይ ከአጭር የህክምና እርዳታ በሁላ ግለስቡ በሽታውን ወደ ሌላ ግለሰብ ከማስተላለፍም ነጻ ይሆናል ማለትም ጭምር ነው። የሕክምና ክትትሉ የሚከናወነው በተላላፊ በሽታ ክፍል በሆስፒታል ውስጥ ነው ፡፡ ሕክምናው አንዴ ከተጀመረና እንደሚሠራ ወይም ስኬታም ውጤን መስጠቱን ከተረጋገጠ በኋላ በዓመት ለአንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ የጥንቃቄ ምርመራውን ማድረግ በቻ በቂ ይሆናል ፡፡ የኤች አይ ቪ ሕክምና ዛሬ በጣም ጥቂት የተጎዳኝ ጉዳቶች ሲኖሩት አብዛኝውም ጊዜም በቀን አንድ ከኒን ብቻ ነው መውሰድም የሚያስፈልገው ።

### የአእምሮ እና ማህበራዊ ድጋፍ

በኤች አይ ቪ ተበካይ ሕሙማን አብሮ ከበሽታው ጋር ለመኖር ከባድ ሁኒታዋች ሊያጋጥማቸው ይችላል ። ምክንያቱም በኅብረተሰቡ ውስጥ ብዙ ጭፍን ጥላቻዎች መኖርና እና እንደዚሁም ስለ ኤች አይ ቪ ያለው ዕውቀት አነስተኛ በመሆኑ ምክነያት ነው ፡፡ ስለሆነም ድጋፍ ሊሰጥዎት የሚችል ሰው መኖራቸው እጅግ አስፈላጊ ነው ፡፡ ይህም ጓደኛ ፣ ቤተሰብ ፣ ሌሎች በኤች አይ ቪ የተበከሉ ሕሙማን ሊሆኑ ይችላሉ ወይም ደግሞ ለምሳሌ ስብሰባዎች ላይ መገኘት ወይንም ኤች አይ ቪ ኖርዌ (HivNorge) ድርጅ መሄድ ይችላሉ ፡፡ በኢንፌክሽን በሽታ ህክምና ክፍሎች ውስጥ ያሉ ሀኪሞች እና ነርሶች ጥሩ ድጋፍ ናቸው ሆኖም ግን ከኤች አይ ቪ ጋር አብረው ከሚኖሩ ግለሰቦችን ጋር መገናኘት በእውነቱ በኤች አይ ቪ የተያዘ ህይወት እንዴት እንደሚመስል የበለጠ ግንዛቤ እና እውቀት ለማግኘት ያስችላል ፡፡ የሂቪ ኖርዌ የአቻ አገልግሎት (HivNorges likepersontilbud) ለኤች አይ ቪ ሕሙማን እና ለዘመዶቻቸው ከሌሎች የኤች አይቪ ሕሙማና ቤተሰቦቻቸው ተገናኝተው ልምድንና ምክርን ለመቀያየር የሚያስችል እድሎችን የሚቀርብ ድርጅት ነው ።

### ሕግ

ከኤች አይ ቪ ጋር ለሚኖሩ ሕሙማን አንዳንድ መብቶች እና ግዴታዎች አላቸው ፡፡ በኢንፌክሽን ቁጥጥር ሕግ ደንቡ መሠረት በኖርዌይ ውስጥ ለኤች አይ ቪ ሕሙማን ሕክምናዎች በነፃ ሲኖን እንደዚሁም ከሚከፈልም የግል ክፍያም ነጻ ነው ፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ለጥርስ ሕክምና የአንዳንድ ወጪዎች ተመላሽ ገንዘብም ማግኘት ይችላሉ ፡፡

ከኤች አይ ቪ ጋር ስለመኖርዎ መረጃ የመስጠት ግዴታ የለብዎትም ፡፡ ሁንም ለሐኪምዎ ግልጽ እንዲሆኑ እንመክራለን ፡፡ ሐኪሙ ጤንነትዎን በጥሩ ሁኔታ መከታተል እንዲችል እና እንዲሁም የሚሰጥዎ ሌላ ህክምና በኤች አይ ቪ መድኃኒቶች ላይ ተጽዕኖ የማያሳድር መሆኑን ለማረጋገጥ ሐኪሙ የታካሚውን የኤች አይ ቪ ምርመራ ማወቁ አስፈላጊ ነው ፡፡

የወንጀል መቅጫ ሕግ አንቅጽ 237 በሰዎች መካከል ከባድ ተላላፊ በሽታዎችን በሰዋች መካከል ስለማስተላለፍ ይገልጻል ፡፡ ስለ ተላላፊ በሽታ ማስተላለፍ እና አንድን ሰው ለበሽታው መተላለፍ በማጋለጥ ላይ ያተኮረ ነው ። ነገር ግን ተላላፊ በሽታው ሊተላለፍ የሚችልበት በቂ እና ግልጽ አደጋ ባለበት ወቅቶች ላይ ብቻ ነው ፡፡ አንድን ሰው ለኤ ች አይ ቪ ተላላፊ በሽታ ማጋለጡ በዚህ አንቀጽ ስር ሊያስቀጣው ይችላል ። ሆኖም ግን ብዙ ልዩ ከዚህ አንቀጽ ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች አሉ ፡፡

- ሕመተኛው ስኬታማ ህክምና ላይ ከሆነ ለሌሎች በበሽታው የማስተላለፍ አደጋ የለውም ፡፡ በጾታዊ ግንኙነት ወቅቶች በሽታው እንዳይተላለፍ ለመከላከል የሚቻለውን ሁሉ ካደረጉ ከቅጣት ነፃ ይሆናሉ ፡፡ ይህ ማለትም በኤች አይ ቪ ሕሙማን በሕክምና ላይ ያሉ ወይም ኮንዶም የሚጠቀሙ ሰዎች ሊቀጡ አይችሉም ማለት ነው፡፡
- ሕመምተኛው የወሲብ አጋሩ በሽታው እንዳለበትና ማስተላልፍ እንደሚችል አውቆ ወይንም ለተላላፊ በሽታ መጋለጡን ፈቅዶ ከሆነ ህመምተናው አይቀጣም ። ይህ ማለት ደግሞ የማሳወቅ ግዴታ አለበት ማለት አይደለም ነገር ግን የወሲብ አጋሩ የሁኔትው መግለጫን አግኝቶ ግን "ራሱን ለተላላፊው በሽታው የተጋላጭነት አደጋ ላይ ከዳረገ " ሕመምተኛው በሽታን በአስተላላፊነት ሊቀጣ አይችልም ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ህክምና ላይ ካልሆነ እና ተላላፊው በሽትውን ከምስተላለፍ ለመከላከል ሌሎች አስፈላጊ እና በቂ እርምጃዎችን የማይወስድ ከሆነ በሕግ ሊቀጣ ይችላል ። በዚህ ሁኔት ተላላፊው በሽታ ተላለፎ ወይም ሳይተላለፍ ቢሆንም እንኳን ያስቀጣል። ለወሲብ ጓደኛው ካላሳወቀ ግለሰቡ በሕግ ሊቀጣ ይችላል።
- የሴትኛ አዳሪዎች እና በመርፌ አደንዛዥ እፆችን የሚወስዱ እንዲሁም ከእናት ወደ ልጅ የሚተላለፍ በሽታን ከአስተላላፉ ከቅጣት ሁሉም ነፃ ናቸው ፡፡

### መድሕን ወይም ዋስትና

መድሕን በሚገቡበት ጊዜ የጤና መረጃ እንዲያቀርቡ የሚጠይቁ አንዳንድ የመድሕን ዓይነቶች አሉ ፡፡ ከነዚህም መካከል የሕይወት እና የአካል ጉዳት መድሕኖ ናቸው ፡፡

ከጤና ጋር የተዛመደ መድሕን ሲገቡ የጤና ሁኔታን መግለጫ እንዲሞሉ ይጠየቃሉ ፡፡ ይህ የሚያቀርቡት የጤና መረጃ ኩባንያው የግለሰቡን የጤና ሁኔታ ግምገማ የሚመስርትበት በመሆኑ ነው፡፡ መረጃው ለመድሕንዎ ትክክለኛ ዋጋ እና የውሎች መስፈርትን ለመወሰን ጥቅም ላይ ይውላል ፡፡ ለኢንሹራንስ ወይም መድሕን የሚያመለክት ማንኛውም ግለሰብ እንደዚህ ያለ የጤና መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት ፡፡ መረጃው ትክክል ካልሆነ ግን መድሕን የተገባበት ሁኔታ ከተከሰተ ካሳ የመድሕን ኩባንኛው አይከፍልም፡፡ የጤና መረጃዎች ምን ግዜም በጥብቅ ጥንቃቄ ይያዛሉ ፡፡

በኤች አይ ቪ ሕሙማን እንድዚሁ የሕይወት እና የአካል ጉዳት መድሕን እንደማንኛውም ግለሰብ መድሕን መግባት ይችላሉ ፡፡ አደጋው በግለሰቡ የግል ሁኔታዊ ግምቶች ላይ በመሠረት ይሰላል። ይህ ማለት ደግሞ ከከባድ የጤና ችግሮች ጋር የሚታገሉ ሰዎች መድሕን ለምግባት ከፍ ያል ችግር ሊጋጥማቸው ይችላል ማለት ነው ፡፡ ነገር ግን ስኬታማ ህክምና በፍጥነት የወሰዱ ግለሰቦች ግን በመደበኛ የሆነ መድህን ወይም ኢንሹራንስ እንደ ማንኛውም ግለሰብ መግባት ይችላሉ ወይም ደግሞ ከፍ ያለ የመድህን ክፍያ በመከፈል መግባት ይችሉ ይሆን ይሆናል።

### ሌሎች ዋስትናዎች ወይም መድህኖች

ኤች አይ ቪ ለሌሎች ኢንሹራንሶች ሊያመጥ የሚችለው ችግሮችን በሚመለከት ሁኔትው እንዲገለጽ የሚጠየቀው ዋስትናው በጤና ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ላላቸው ኢንሹራንሶች ወይም ዋስትናዎች ብቻ ነው። ለእንደዚህ አይነት ዋስትናዎች የጤና የምስክር ወረቀቶችን መጠየቅ ይፈቀዳል፡፡ ይኸውም ለየሞት አደጋ መድሕን ፣ የአካል ጉዳት አደጋ መድሕን ፣ የሕክምና መድሕን ፣ የጤና መድህን ፣ በሕመም መቅረት የሚጋለግል መድሕን እና የአደገኛ የሕመም አደጋ መድህን ናቸው ፡፡

የይዘቶች መድሕን እና የጉዞ መድን በሚገቡበት ጊዜ የጤና መግለጫን ማግኘት ጠቃሚ አይሆንም ፡፡ አብዛኛዎቹ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች እንዲሁ ለአደጋ መድሕን የጤና መግለጫን አይጠይቁም ፡፡ የአደጋ መድሕን የግል ሕይወት መድሕን ነው ስለሆነም የሕይወት አደጋ መድሕን አይደለም ስለዚሕ የጤና የምስክር ወረቀት መጠየቅ ከሚችሉበት ዋስትናዎች ጋር በተመሳሳይነት በአንድ ቡድን ውስጥ ይገኛል ፡፡ ሆኖም የጤና መረጃ ለእንዲህ ዓይነቱ መድሕን ጠቃሚ አይሆንም ፣ ስለሆነም ከአደጋ መድሕን ጋር በተያያዘ የጤና መረጃን መጠየቅ አይፈቀድም ፡፡

### የጉዞ መድህን

ወደ የጉዞ ዋስትና እና ስለ ኤች አይ ቪ መድሕን በሚመጣበት ጊዜ አግባብ ያለው ጠንቅ ያለ አስተሳሰብን መያዙ ጠቃሚ ነው ፡፡ በደንብ የሕክምና ክትትል የሚሰጠው የኤችአይቪ ኢንፌክሽን ሕመምተኛ ከሆኑና እና በኖርዌይ ውስጥ የሕክምና ክትትልን የሚያገኙ ከሆነ እና በጉዞው ወቅቶች የተረጋጋ ሁኔት ላይ ከአሉ በኤች አይ ቪ በሽታ ድንገተኛ ወይም ያልተጠበቀ ለውጥ ከተከሰተ የመድሕን ክፍያን ወጭዎችን መሸፍንን ያገኛሉ ፡፡
የጉዞ መድህን የማይሸፍነው በኤች አይ ቪ ጋር በተዛመደ ምክንያቶች በተደጋጋሚ ሆስፒታል በመግባት የጤና እርዳታ የሚወስዱ ከሆነና እንደዚሁም ከመጓዝ በቅርብ ጊዜ በፊት የሚወሰዱት የመድኃኒት ላይ ለውጥ ከአደረጉ ነው። ይኸም ሕክምናዊ ወይም አገልግሎታዊ ነገሮች ላይ የተመሰረትም ሁኒታም ቢሆንም ነው ።

### ኤች አይ ቪ ኖርዌ (HivNorge)

ከኤች አይ ቪ ሕመም ጋር ቀጥታ ግኑኝነት በአለው ነገሮች ላይ ሕጋዊ ጥያቄ ከአሎት ወይም የሕግ አገልግሎት ማግኘት ከአስፈለግዎች ኤች አይ ቪ ኖርዊ ሊረዳዎች ይችላል ። በተጨማሪም የአጠቃል ምክር የመስጥትን አገልግሎትን ስለምናቀርብ ከኤች አይ ቪ የተያያዙ ሌሎች ጥያቄዎች ካሉዎት በምክር ልንረዳዎች እንችላለን።

ኤች አይ ቪ ኖርዌ ከኤችአይቪ ጋር ለሚኖሩ ሕሙማን ወይም በኤች አይ ቪ ጋር በምንኛውም መንገድ የተያያዥነት ያላቸው ሰዎች ሁሉ እንደዚሁም ፒአር ኢፒ (PrEP) ተጠቃሚያትን ጨምሮ ሕክምናዊ አገልግሎት የማይሰጥ የውይይት አገልግሎት አቅርቦት አለን ። ከኬሚሜፍሪንድሊ (Chemfriendly)ድርጅት ጋር በመተባበር ለኬሚክስ ወሲብ ተጠቃሚዎች (chemsexbrukere) እና ለሌሎች አደንዛዥ እጽ ለሚጠቀሙ ለግብረ ሶደማውያን የውይይት አቅርቦት አገልግሎትም እንሰጣለን ። የአስተርጓሚ ሚያስፈልግ ከሆነ አብረን በአንድ ላይ ከገመገምን በሆላ እንዳአስፈላጊነቱ ይቀርባል ።

በተጨማሪም በኤች አይ ቪ ሕሙማንና ከኤች አይ ቪ ጋር ለሚኖሩ ግለሰቦች ወይም ከኤች አይ ቪ በሆን መንገዱ ውስጥ የተያያዙ ግለሰቦች ፣ለፐራይፐ ተጠቃሚዎች (PrEP-brukere) እና ለሌሎች ፍላጎት ላላቸው ወገኖች ብዙ ሊካፈሉባቸው የሚችሉት እንቅስቃሴዎችን አሉን ። ለአቅርቦታችን እና ለእንቅስቃሴዎቻችን ለማወቅ እንዲችሉ [የቀን መቁጠሪያችንን](kalender) ([kalender]) ይከታተሉ።

ከኤች አይ ቪ ጋር ከሚኖር ሌላ ሕሙማን ወይም ግለሰብ ጋር ለመነጋገር ከፈለጉ እኛ ለመወያየት ደስተኛ የሆኑ እና ተመሳሳይ ሁኔት ላይ የሚገኙም ግለሰቦችም አሉን ።በተመሳሳይ ሁኔት ላይ የሚገኙት ግለሰቦች እንዲሁም በተጨማሪ በርካታ ቋንቋዎችን የሚናገሩም ናቸው ።ኤች አይ ቪ ኖርዌን (HivNorge) በስልክ ቁጥር 21314580 ፣ በኢሜል (e-post)ወይም በፌስቡክ ገፃችን(Facebook-side)ማግኘት ይቻላል ።

### ድጋፍ የት ማግኘት ይችላል

በአጠቃላይ በኖርዌይ ውስጥ በኤች አይ ቪ ለተያዙ ሕሙማን አገልግሎት የሚሰጡ በርካታ ድርጅቶች አሉ ። ከዚህ በታች የተወሰኑት እርዳታ የሚሰጡ ድርጅቶች ምሳሌዎች ተጠቅሰዋል ። በእነዚህ ሁሉ በተጠቀሱት ድርጅቶች በሙሉ ልዩ ባለሙያዎችን በማግኘት ወይም ከሌሎች ኤች አይ ቪ ጋር ከሚኖሩ ገለሰቦች ጋር ለመገናኘት እድል ያገኛሉ።

ኦስሎ (Oslo ): HivNorge og Aksept
በርገን (Bergen): Leve med hiv, Kirkens bymisjon Bergen
ሀውገላንድ (Haugalandet): Leve med hiv Kirkens bymisjon Haugesund
ትሮንዳይም (Trondheim): Aksept og mestring, Kirkens bymisjon Trondheim
ክሪስቲያንሳንድ (Kristiansand): Sørlandet sykehus, HIV-poliklinikken
ትርምሶ (Tromsø): UNN infeksjonsposten og Sosialmedisinsk senter i Tromsø

በተጨማሩ Zanzu.no ድኽረ ገጽ መግለጫዎችን ስል ሰውነት አካላት፣ ስለ ጤና፣ስለ ወሲባዊ ጤነትን በሚመለከት እና ስለ ኤች አይ ቪ በተለያየ ቋንቋ ተጽፈው ያገኙሉ።

### ኤች አይ ቪ እና ስል ኮቪድ- 19 (Hiv og Covid-19)

ከኤች አይ ቪ ሕሙማን በመሆን በሚኖሩበት ጊዜ በኮሮና ቫይረስ የመጠቃት ወይም በኳቪድ -19 መበከል ከባድ የህመም አደጋ የተጋለጡ አይደሉም ። ዝቅተኛ የሆነ የበሽታ የመከላከል አቅም ካለዎት (ማለትም ከ 200 ሲዲ 4 ቆጠራዎች በታች ወይም (dvs. under 200 CD4-tall)) እና ሌሎች ተጨማሪ ከባድ በሽታዎች ከአለበዎት ግን ልመጠቃት ከፍተኛ የሆነ ተጋላጭነት ሊኖርዎት ይችላል ።

በኖርዌይ በሚገኙ ሆስፒታሎች ውስጥ ተላላፊ በሽታን የሚያክሙ ክፍሎች ናቸው የኳረናን ሕሙማንን የሚያክሙ ይክው ክፍል ነው ። ስልሆነው በአሁኑ ጊዚያቶች አብዛኛውን ጊዜ እጅግ በጣም የበዛ የሰራ ጫና አለባቸው ። በዚህም ምክነያት የኤች አይ ቪ ህሙማን ተገቢውን የሕክምና ክትትል በተገቢው መንገድ ላያ ገኙ ይችላሉ ። ስለ ሆነም አንዳንዱ የጤና ክትትል በአካል በመገኘት ሳይሆን በስልክ ወይም በዲጅታል በኩል ሊሰጥ ይቻል ይሆናል።

የኤች አይ ቪ ኖርዌ (HivNorge) በተለያተለያዩ ቋንቋዎች ስለ ኤች አይ ቪ እና ስል ከኳቪድ- 19 (hiv og covid-19 på flere språk )መግለጫዎችን አውጥተዋል ።